ቁጥር፡-ሕ/ም/ማ/ማ/ዳ.....4486...../18

ቀን፡- 29/12/2018 ዓ.ም.

ለአብክመ ገቢዎች ቢሮ

ባህር ዳር

ጉዳዮ፡ <u>የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል</u>

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ. ም. እና በዚህ አዋጅ ማሻሻያ መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አስመልክቶ አዋጁ በወጣ በ2 (ሁለት) ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህም መሠረት ቢሯችሁም በቁጥር ገቢዎችም.ቢ/3.8/265 በቀን 27/11/2018 ዓ.ም. በተጻፈ ሽኝ ደብዳቤ "የግብር ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ የጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር አገቢ 30/2017 ተብሎ የተገለጸውን እንድንመዘግብላችሁ የላካችሁልን መሆኑ የሚታወቅ ነው።

በእኛም በኩል የተላከልንን ይህን መመሪያ በአዋጁ መሠረት ከተመለከትን በኃላ፣ በክልል ደረጃ "የግብር ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ የጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 175/2018 ዓ.ም." በሚል መዝግበነዋል።

በመሆኑም መመሪያውን በተመዘገበው ቁጥር መሰረት ሥራ ላይ እንዲውል እየገለጽን፣ የመዘገብነውን 6 ገጽ መመሪያ በዚህ ሽኝ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ መሆኑን እናሳውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

መስፍን መኮነን

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

ዐቃቤ ሕግ

<u>ግልባጭ</u>

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክት ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  <u>ፍትህ ቢሮ</u>

ቀ ሀ

የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ

የግብር ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ የጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 175/2018 ዓ.ም

ማንኛውም ታክስ ከፋይ እራሱ አዘጋጅቶ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ የገቢዎች ቢሮ ሲፈቅድለት ሊያሻሽል እንደሚችል በአዋጁ የተደነገገ በመሆኑ እና፣

የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለማሻሻል በታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ሲቀርብ ማሻሻያው ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ግልጽ አሠራር ማስቀመጥ በማስፈለጉ፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 29(3) እና 135(3) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የግብር ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ የጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 175/2018 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1/ "የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማሻሻያ ጥያቄ" ማለት ታክስ ከፋዩ በራሱ አዘጋጅቶ ባቀረበው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎች እና ምክንያቶቹን በመግለጽ የሚያቀርበው የማሻሻያ ጥያቄ ነው።

2/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በተወሰነ አካባቢ በግብር ከፋዮች በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ማለትም በተፈጠረ ጦርነት፣ በንግድ ስራ ላይ ጫና የሚፈጥር ጦርነት፣ ጎርፍ፣ ቃጠሎ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች ወይም ሌላ ተመሳሳይ ክስተት ሲያጋጥም ነው።

3/ "ቦርድ" ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎች ድንጋጌ መሠረት የውጭ ኦዲተሮች የሚያዘጋጁትን የሂሳብ ሪፖርት መርምሮ ማረጋገጫ የሚሰጥ የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ ኦዲት ቦርድ ነው።

4/ "ገቢዎች ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ማለት ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ የገቢ ተቋማትንም ይጨምራል።

5/ "ኃላፊ" ማለት የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም ሚወክለው የሥራ ኃላፊ ወይም በየደረጃው የሚገኝ የገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ ነው።

6/ "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው።

7/ "ደንብ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2010 ነው።

8/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች እንደሁኔታው በታክስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

9/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናል።

3. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻልለት ጥያቄ በሚያቀርብ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የራስ ታክስ ስሌት ስለሚሻሻልበት ምክንያትና አቀራረብ

4. የራስ ታክስ ስሌት የሚሻሻልበት ምክንያት፣

1/ ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻልለት ሲያመለክት በሚከተሉት ምክንያቶች ገቢዎች ቢሮ ሊያሻሽልለት ይችላል፡-

ሀ) የሂሳብ ስሌት ስህተት፣

ለ) የገቢ እና ወጪ አመዘጋገብ ስህተት፣

ሐ) ከሒሳብ መደብ አመራረጥ(Chart of Account) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲኖር፤

መ) የጆርናል ምዝገባ ስህተት ሲኖር፤

ሠ) ሂሳብ ወደ ሌጀር ሲተላለፍ የተከሰተ ስህተት ሲያጋጥም፤

ረ) ከሒሳብ ማስተካከያ (Adjusting Entry) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲያጋጥም፤

ሰ) በሒሳብ መዘገብ ላይ ሳይመዘገብ የተዘለለ የገቢና ወጪ ሰነድ ሲኖር፤

ሸ) የሃብትና ቆጠራ አያያዝ ስህተት፣

ቀ) የሒሳብ አያያዝ ዘዴ ስህተት ፣

በ) በውጭ አዲተሮች እና በቦርዱ በቀረበ የአዲት ምርመራ ሪፖርት የቀረበ ማስተካከያ፣

ተ) ሦስተኛ ወገን በሚሰጠው ማረጋገጫ ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት በሂሳብ መዝገቡ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ሲያስፈልግ ፤

ቸ) በታክስ ሕግ ያልተፈቀደ ወጪ በተቀናሽነት በመያዙ ምክንያት የተፈጠረ ስህተት፤

ኀ) የግልና የንግድ ሒሳቦች በመቀላቀላቸው የተፈጠረ ስህተት ሲያጋጥም፤

ነ) በታክስ ማስታወቂያ ቅጽ ላይ የአመዘጋገብ ወይም የአገላለጽ ስህተት ሲያጋጥም፣

ኘ) በታክስ ወይም በተለይ በኤክሳይዝ ታክስ ሂሳብ አያያዝ ላይ የማምረቻና አስተዳደራዊ ወጪ ተፋልሰውና ባልተገባ ቦታ ላይ ተመዝግበው ሲገኙ፣

አ) ከተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከኤክሳይዝ ታክስ ጋር በተያያዘ በታክስ ማስታወቂያ ውስጥ ሳይካተት የቀረ ታክስ ወይም ከተቀናሽ ሂሳብ አያያዝ እና ተመላሽ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ስህተት ሲያጋጥም፣

ከ) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለታክስ ስሌት የሚያስፈልጉ ሰነዶች ሳይሟሉ በመቅረታቸው ታክስ ከፋዩ በእጁ ያሉትን ሰነዶች ብቻ መሠረት በማድረግ አሳውቆ ከከፈለ በኋላ የተሟላ ሰነድ ማቅረብ በቻለበት ጊዜ፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች የተለየ እና በሚከፈለው የታክስ መጠን ላይ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብ የገቢዎች ቢሮ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል።

5. <u>የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1/ ታክስ ከፋይ ያቀረበው የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻልለት በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ የታክስ ስሌቱን ለማሻሻል ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በዝርዝር በመጥቀስ ጥያቄውን በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ለገቢዎች ቢሮ ማቅረብ አለበት፤

2/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን በፊት ባሉ 5 ዓመታት የግብር ዘመን ጊዜ ውስጥ በነበሩ የራስ ታክስ ስሌቶች ላይ ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ የሁሉንም የግብር ዘመናት የታክስ ስሌት ማሻሻያ በአንድነት ሊያቀርብ ይችላል።

6. <u>የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማመልከቻው ይዘት፣</u>

1/ በራስ ታክስ ስሌት ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል።

ሀ) የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ የተጠየቀበትን የታክስ ዓይነት እና የሂሳብ ጊዜ፣

ለ) ማሻሻያ የሚደረግበት ጉዳይ እና ምክንያቱን፤

ሐ) ማሻሻያ እንዲደረግበት የተጠየቀው ጉዳይ የሚያስከትለው የገንዘብ ወይም ሌላ ለውጥ፣

መ) በሚሻሻለው የታክስ ስሌት የተገለጸው የታክስ መጠን ወይም ወደፊት የሚሸጋገር ኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለ የግብዓት መጠን የሚገልጽ መሆን አለበት።

2/ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል የሚቀርበው ማመልከቻ የማሻሻያ ምክንያቶችን ከሚደግፉ አስፈላጊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

7. ማመልከቻው የሚቀርብበት ጊዜ

1/ ታክስ ከፋዩ የራስ የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ለገቢዎች ቢሮ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችለው የመጀመሪያ የራስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ ከፋዩ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ከሆነ ወይም በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገበ የሚይዝ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ከሆነ የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል ለገቢዎች ቢሮ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችለው የመጀመሪያው የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው።

8. የውሳኔ አሰጣጥ

ገቢዎች ቢሮ፡-

1/ የቀረበለትን የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ማመልከቻ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ባሉት 120(አንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ክፍል መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

2/ በቀረበለት ማመልከቻ መሠረት የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ የፈቀደ እንደሆነ የታክስ ስሌቱን በማሻሻል ለታክስ ከፋዩ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ይሰጣል፤

3/ የቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ በጹሁፍ ለታክስ ከፋዩ ያሳውቃል፤

4/ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ አዲት እየተደረገ ባለበት ጊዜ፣ ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣ የቀረበው ማመልከቻ አዲት እያደረገ ላለው የሥራ ክፍል ተመርቶ ተገቢው ውሳኔ ከአዲት ውጤቱ ጋር ይሰጠዋል።

9. የራስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በድጋሜ ስለማሻሻል

ገቢዎች ቢሮ ታክስ ከፋዩ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል ወስኖ የተሻሻለውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 28/3 (ለ) መሠረት ለታክስ ከፋዩ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከመስጠት አያግደውም።

10. የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ የሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

1/ ገቢዎች ቢሮ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ካወጣ በኋላ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፤

2/ አንድ ጊዜ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበት የራስ ታክስ ስሌት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት የታክስ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በድጋሚ ማሻሻያ እንዲደረግበት የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው ቢኖርም ገቢዎች ቢሮ በራሱ ተነሳሽነት የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው ይችላል።

11. የተሻረ መመሪያና ተፈጻሚነት የሌላቸው አሰራሮች

1/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር አገቢ 10/2011 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

2/ ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም አሰራር መመሪያው በሚሸፍነው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

12. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ነው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለጸው ቢኖርም፣ ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ባህር ዳር

ክብረት ማህሙድ ሁሴን

ቢሮ ሃላፊ